# በክርስትና መሰረታዊ ትምህርት ላይ የሚነሱ ቁርዓናዊ ትችቶች

1. የትምህርተ ስላሴ ተዓማኒነት
2. የኢየሱስ ክርስቶስ ልጅነት እና አምላክነት
3. የመጽሀፍ ቅዱስ ተዓማኒነት

# የትችቶቹ ምንጭ ምንድናቸው

1. የእስልምና አሀዳዊ የአምላክ ግንዛቤ
2. ስለአምላክ ቃል ምንነት እና አመጣጥ ላይ ያለ ግንዛቤ
3. የነቢዩ መሀመድ ሚና ላይ ያለ ግንዛቤ
4. የእስልምና ሸዐዳ/ የእምነት መግለጫ

“በል እርሱ አላህ አንድ ነው መሀመድም የእርሱ መልዕክተኛ ነው”

# ትምህርት ስላሴ፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ልጅነት እና አምላክነት

# ትምህርተ ስላሴንና የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት የሚቃወሙ ክፍሎች

**ሱረቱል አል-ማኢዳ 5 ፡ 73-75**

እነዚያ **«አላህ የሦስት ሦስተኛ ነው»** ያሉ በእርግጥ ካዱ፡፡ ከአምላክም አንድ አምላክ እንጅ ሌላ የለም፡፡ ከሚሉትም ነገር ባይከለከሉ ከነሱ እነዚያን የካዱትን አሳማሚ ቅጣት በእርግጥ ይነካቸዋል፡፡ ወደ አላህ አይመለሱምና ምሕረትን አይለምኑትምን? አላህም መሓሪ አዛኝ ነው፡፡ **የመርየም ልጅ አልመሲሕ ከበፊቱ መልክተኞች በእርግጥ ያለፉ የኾነ መልክተኛ እንጅ ሌላ አይደለም፡፡ እናቱም በጣም እውነተኛ ናት፡፡ (ሁለቱም) ምግብን የሚበሉ ነበሩ፤** አንቀጾችን ለነርሱ (ለከሓዲዎች) እንዴት እንደምናብራራ ተመልከት ከዚያም (ከእውነት) እንዴት እንደሚመለሱ ተመልከት፡፡

# የቀጠለ.........

## ሱረቱል አል-ማኢዳ 5 ፡ 116

አላህም፡- «የመርየም ልጅ ዒሳ ሆይ! አንተ ለሰዎቹ፡- **እኔንና እናቴን ከአላህ ሌላ ሁለት አምላኮች አድርጋችሁ ያዙ ብላሃልን?»** በሚለው ጊዜ (አስታውስ)፡፡ «ጥራት ይገባህ፤ ለእኔ ተገቢዬ ያልኾነን ነገር ማለት ለኔ አይገባኝም፡፡ ብዬው እንደ ኾነም በእርግጥ ዐውቀኸዋል፡፡ በነፍሴ ውስጥ ያለውን ሁሉ ታውቃለህ፡፡ ግን አንተ ዘንድ ያለውን አላውቅም፡፡ አንተ ሩቆችን ሁሉ በጣም ዐዋቂ አንተ ብቻ ነህና» ይላል፡፡

# የቀጠለ…………

## ሱረቱል አሊ-ዒምራን 3 ፡ 45-49

መላእክት ያሉትን (አስታውስ)፡- «መርየም ሆይ! አላህ ከርሱ በኾነው ቃል ስሙ አልመሲሕ ዒሳ የመርየም ልጅ በዚህ ዓለምና በመጨረሻውም ዓለም የተከበረ ከባለሟሎችም በኾነ (ልጅ) ያበስርሻል፡፡» **«በሕፃንነቱና በከፈኒሳነቱ ሰዎቹን ያነጋግራል፡፡** ከመልካሞቹም ነው» (አላት)፡፡ ጌታዬ ሆይ! ሰው ያልነካኝ ስኾን ለኔ እንዴት ልጅ ይኖረኛል? አለች፡፡ ነገሩ እንዳልሽው ነው፡፡ **አላህ የሚሻውን ይፈጥራል፡፡ አንዳችን በሻ ጊዜ ለርሱ ኹን ይለዋል፤ ወዲውኑም ይኾናል አላት፡፡** ጽሕፈትንና ጥበብንም ተውራትንና ኢንጂልንም ያስተምረዋል፡፡ ወደ እስራኤልም ልጆች መልክተኛ ያደርገዋል፡፡ (ይላልም)፡- «እኔ ከጌታዩ ዘንድ በተዓምር ወደ እናንተ መጣሁ፡፡ **እኔ ለናንተ ከጭቃ እንደ ወፍ ቅርፅ እፈጥራለሁ፡፡ በርሱም እተነፍስበታለሁ፡፡ በአላህም ፈቃድ ወፍ ይኾናል፡፡** በአላህም ፈቃድ ዕውር ኾኖ የተወለደን፣ ለምጸኛንም አድናለሁ፡፡ ሙታንንም አስነሳለሁ፡፡ የምትበሉትንና በቤታችሁ የምታደልቡትንም ሁሉ እነግራችኋለሁ፡፡ የምታምኑ እንደኾናችሁ ለእናንተ በዚህ ውስጥ በእርግጥ ተዓምር አለበት፡፡»

# የቀጠለ............

**ሱረቱል አሊ-ዒምራን 3 ፥ 59**

አላህ ዘንድ የዒሳ ምሳሌ እንደ አዳም ብጤ ነው፡፡ **ከዐፈር ፈጠረው፡፡** ከዚያም ለርሱ (ሰው) **«ኹን»** አለው፤ ኾነም፡፡

# ማጠቃለያ፡ አስተምህሮተ ስላሴ እና የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት

1. ስላሴ ማለት የሶስት ሶስተኛ ማለት ነው
2. ማሪያም በክርስትና አስተምህሮ ውስጥ እንደ መከኮትነት ተሰይማ ታውቃለች
3. መብላትና መጠጣት የአምላክ መገለጫዎች አይደሉም
4. ኢሳ መለኮት አለመሆኑን በቁርዓን ውስጥ ተናግሯል
5. ኢሳ እንደ አዳም የሆነ ሰው ነው
6. ኢሳ የተፈጠረ ፍጡር ነው

# ትምህርተ ስላሴ እና የኢየሱስ ክርስቶስ ልጅነት በቁርዓን እይታ

**ሱረቱል አል-ኢኽላስ 112 ፥ 1-4**

በል «እርሱ አላህ አንድ ነው፡፡ «አላህ (የሁሉ) መጠጊያ ነው፡፡ **«አልወለደም፤ አልተወለደምም፡፡ «ለእርሱም አንድም ብጤ የለውም፡፡»**

**ሱረቱል አል-ሙእሚኑን 23 ፥ 91**

**አላህ ምንም ልጅን አልያዘም (አልወለደም)፡፡** ከእርሱም ጋር አንድም አምላክ የለም፡፡ **ያን ጊዜ (ሌላ አምላክ በነበረ) አምላክ ሁሉ በፈጠረው ነገር በተለየ ነበር፡፡** ከፊላቸውም በከፊሉ ለይ በላቀ ነበር፡፡ አላህ ከሚመጥኑት ሁሉ ጠራ፡፡

# የቀጠለ

**ሱረቱል አል-አንአም 6 ፡ 101**

(እርሱ) ሰማያትንና ምድርን ያለ ብጤ ፈጣሪ ነው፡፡ ለእርሱ **ሚስት የሌለችው ሲኾን እንዴት ለእርሱ ልጅ ይኖረዋል?** ነገርንም ሁሉ ፈጠረ፡፡ እርሱም ነገሩን ሁሉ ዐዋቂ ነው፡፡

**ሱረቱል አል-አንቢያ 21 ፡ 17**

መጫወቻን (ሚስትና ልጅን) ልንይዝ በሻን ኖሮ **ከእኛ ዘንድ በያዝነው** ነበር፡፡ (ግን) ሠሪዎች አይደለንም፡፡

**ሱረቱል አል-ጂን 72 ፡ 3**

‹እነሆም የጌታችን ክብር ላቀ፡፡ **ሚስትንም ልጅንም አልያዘም፡፡**›

# ማጠቃለያ፡ አስተምህሮተ ስላሴ እና የኢየሱስ ልጅነት

1. ሁለት አምላክ ካለ አንዱ ካንዱ መብለጡ አይቀሬ ነው
2. አላህ ልጅ ካለው ልጁም አምላክ መሆኑ አይቀሬ ነው
3. አላህ ልጅ እንዲኖርው የግድ ሚስት ያስፈልገዋል

# ከላይ የተጠቀሱትን ክፍሎች ለምን መመልከት አስፈለገን?

1. የእስልምና እምነት ተከታዮች በክርስትና አስተምህሮ ላይ የሚያነሷቸው ጥያቄዎች መጽሀፍ ቅዱስን አንብቦ ካለመረዳት የመነጬ ሳይሆን ቁርዓን አስተምህሮዎቹን ስሁት በሆነ መንገድ ስለተቃወማቸው መሆኑን እንድንገነዘብ
2. ለአንድ ሙስሊም የመጽሀፍ ቅዱስ አስተምህሮ እውነት መሆን የቁርዓንን ወሸተኝነት ስለሚያረጋግጥ በሚችሉት ሁሉ የመጽሀፍ ቅዱስን ትምህርት መቃወም አስፈላጊ መሆኑን እንድንገነዘብ
3. የመጽሀፍ ቅዱስ እውነትም ውሸትም መሆን ቁርዓንን ውሸት እንደሚያሰኙት እንድንረዳ

# ስለስላሴ እና ስለ ክርስቶስ ከሙስሊሞች ጥያቄዎችን ስንጠየቅ አስከትለን መጠየቅ ያለብን

1. መጽሀፍ ቅዱስ ስላሴ ማለት የሶስት ሶስተኛ ነው ብሎ ያስተማረው በተትኛው ክፍሉ ነው?
2. አምላክ ለመሆን አለመመገብ ማሳያ ከሆነ የማይበላ ነገር ሁሉ አምላክ ነው ማለት ነው?
3. ቁርዓን በየትኛው ክፍሉ መጽሀፍ ቅዱሳዊውን የስላሴን ትምህርት ተችቶ ያውቃል?
4. ቁርዓን ለምን መጽሀፍ ቅዱስ ያላስተማረውን የስላሴን ትምህርት እንዳስተማሩ በማሰብ ክርስቲያኖችን ይከሳል?
    1. አላህ፣ ኢሳ እና ማሪያምን እንደስላሴ መውሰዱ ተገቢ ነው?
5. ቁርዓን የኢየሱስ ልጅነትን ለምን መጽሀፍ ቅዱሳዊ ባልሆነ አስተምሮተ ልጅነት መስሎ ክርስትናን ይከሳል?
6. አላህ ልጅ እንዲኖርው የግድ ሚስት ያስፈልገዋል የሚለው አስተሳሰት ትክክለኛ አስተሳሰብ ነው? በዚህ ሚዛን መጽሀፍ ቅዱስን መመዘን ተገቢ ነው?
7. ቁርዓን ለምን ክርስቲያኖች በትክክል የሚያምኑትን ነገር ገልጾ እንዲህ ማመናችሁ ስሁት ነው ማለት አቃተው?

# የመጽሀፍ ቅዱስ ተዓማኒነት ላይ የሚነሱ ክሶች

- እውነትን ከውሸት ጋር በመቀላቀል፡- ሱረቱል አል-በቀራ (የላም ምዕራፍ) 2፡ 40-42፣ ሱረቱል አሊ-ኢምራን (የዒምራን ቤተሰብ ምዕራፍ) 3 ፡ 71፣
- እውነቱን መደበቅ፡- ዋቢ የቁርአን አያዎች ሱረቱል አሊ-ኢምራን (የኢምራን ቤተሰብ ምዕራፍ) 3 ፡ 71፣ ሱረቱል አል-በቀራ (የላም ምዕራፍ) 2 ፡ 42፣ 146
- እውነቱን መሸሸግ፡- ሱረቱል አል-ማኢዳ (የማእድ ምዕራፍ) 5 ፡ 15
- ምላስን ማጣመም፡- ሱረቱል አሊ-ኢምራን (የኢምራን ቤተሰብ ምዕራፍ) 3 ፡ 78፣ ሱረቱል አል-ኒሳእ (የሴቶች ምዕራፍ) 4 ፡ 46
- ቃላትን ከስፍራው መቀየር፡- ሱረቱል አል-በቀራ (የላም ምዕራፍ) 3 ፡ 75፣ ሱረቱል አል-ኒሳእ (የሴቶች ምዕራፍ) 4 ፡ 46፣ ሱረቱል አል-ማኢዳ (የማእድ ምዕራፍ) 5 ፡ 41

# የመጽሀፍ ቅዱስ ተዓማኒነት ላይ የሚነሱ ክሶች

# አስባባዊ ምላሽ

# እውነትን ከውሸት ጋር መቀላቀል እና እውነቱን መደበቅ

**ሱራ 2፡40 42**

የእስራኤል ልጆች ሆይ! ያችን በናንተ ላይ የለገስኳትን ጸጋዬን አስታውሱ፡፡ በቃል ኪዳኔም ሙሉ፤ በቃል ኪዳናችሁ እሞላለሁና፤ እኔንም ብቻ ፍሩ፡፡ ከናንተ ጋር ያለውን (መጽሐፍ) የሚያረጋግጥ ሆኖ ባወረድኩትም (ቁርኣን) እመኑ፡፡ በርሱም የመጀመሪያ ከሓዲ አትሁኑ፡፡ በአንቀጾቼም ጥቂትን ዋጋ አትለውጡ፡፡ እኔንም ብቻ ተጠንቀቁ፡

**ሱራ 3፡71**

የመጽሐፉ ባለቤቶች ሆይ! እናንተ የምታውቁ ስትኾኑ በአላህ አንቀጾች ለምን ትክዳላችሁ? «የመጽሐፉ ሰዎች ሆይ! እውነቱን በውሸት ለምን ትቀላቅላላችሁ እውነቱንም እናንተ የምታውቁ ስትኾኑ ለምን ትደብቃላችሁ»

# የአንቀጾቹ አስባብ/ የወረደበት ምንክያት ምንድነው?/

ቁርዓኑ የወረደበት አስባብ መጽሀፍ ቅዱስ በጽሁፍ ደረጃ ስለመበረዙ የሚያሳይ አይደለም። አስባቡን ከታች እንደሚከተለው ቀርቧል

አያቶላ መሃዲ ፑያ እና ሰ.ቨ. ሚር አህመድ አሊ በጋራ ባዘጋጁት ተፍሲር ስለ ሱራ 2 ፡ 40-42 እንዲህ ብለዋል፡-

"አይሁዳውያኑን አላህ በቃል ኪዳናቸው ታማኞች እንዲሆኑ ያሳስባቸዋል፤ በዘዳ 26 ፡ 16-17፣ በዘዳ 18 ፡ 5፣ በዘዳ 18 ፡ 18-19 ነቢይ እንደሚያስነሳላቸው ቃል ገብቶላቸው ነበር፤ ይህም የተገባላቸው ቃል ነቢዩ ሙሐመድን ነበር፡፡

ኢብን አባስም ይህንን አንቀጽ ሲያብራራ፡- "“እውነቱንም በውሸት አትቀላቅሉ” ማለት የሙሐመድን መገለጫ ከሐሰተኛው ክርስቶስ መገለጫ ጋር አትቀላቅሉ ማለት ነው" ብሏል፡፡

# የቀጠለ...........

ክርስቲያኖች ይህ የኪዳን ቃል ኢሳ ነው ይላሉ ሆኖም ኢሳ ራሱ በዮሐ 14 ፡ 16፣ 26 እና በዮሐ 16 ፡ 7-14 ባለው ላይ ስለእርሱ እንዳልሆነ ተናግሯል፡፡ **ከቁርአን ቀድሞ በወረደው መጽሐፍ ተገልጾ እያለ ክርስቲያኖች ሌላ ቅርጽ ይሰጡና ይደብቁት ነበር**፡፡ በነቢዩ ሙሐመድ ዘመን የነበሩ ብዙ የአይሁድ **መምህራንም በመጽሐፉ የሰፈረውን እውነተኛውን ቃል ያውቁ ነበር፤**" በማለት አብራርተዋል፡፡

ሌላው አንቀጽ ሱራ 3 ፡ 71 ነው፡፡ ስለዚህ አንቀጽም የተሰጡ ማብራሪያዎች አሉ፡፡ ማብራሪያው ከአንቀጽ 69 ጀምሮ እስከ አንቀጽ 73 ባለው ይጠቃለላል፡፡ ኢብን አባስ ለዚህ አንቀጽ ለሱራ 2 ፡ 42 የሰጠውን ማብራሪያ በቀጥታ ተጠቅሞበታል፤ “የሐሰተኛው ክርስቶስን ባህሪ ከነቢዩ ሙሐመድ ባሕሪ ጋር ለምን ትቀላቅላላችሁ” በማለት፡፡ አንቆቹ የወረዱበትን ምክንያት የዘገቡ አካላትም እንደገለጹት አንቀጾቹ የወረዱት ሙስሊሞችን ከእስልምና ለመመለስ የተደረጉ ጥረቶችን ለመመከት እንደሆነ ይገራሉ፡፡

# እውነቱን መሸሸግ፡- ሱረቱል አል-ማኢዳ (የማእድ ምዕራፍ) 5 ፡ 15

ሱረቱል አል-ማኢዳ (የማእድ ምዕራፍ) 5 ፡ 15

የመጽሐፉ ባለቤቶች ሆይ፤ ከመጽሐፉ ትሸሽጉት ከነበራችሁት ነገር ብዙውን ለእናንተ የሚገልጽ፣ ከብዙውም የሚተው ሲሆን መልእክተኛችን (ሙሐመድ) በእርግጥ መጣላችሁ፡፡ ከአላህ ዘንድ ብርሃንና ገላጭ መጽሐፍ በእርግጥ መጣላችሁ፡፡

كم ْر ى س ُ ولُن ى اي ا ُ ب ى يُّ كمِ ّ لى ُ كث ْ بك ِ ي ْ ًمَّا ِ ّ ّ ا كنت ُ م ْ تُف ُ ُ م وُن ِ ن ى الْكِ ت ى ا و ب ِ ى ي ى ع ْ ف وُ

ى اء ى نْد ج ِ ب ق ا ى ت الْكِ ى ل ْ ا أله ى ي ن ى ع ٍ ي ْ ِ ي ٌ صلى كث ِ ُّ مب ٌ ب ا ى ت كِ ى و ٌ ُ ور ن ِ اللَّه ى ُ كمِ ّ من ى اء ى نْد

- በዚህ አንቀጽ ቁርአን የመጽሐፉ ሰዎች ከሚሸሽጉት ብዙውን የሚገልጽ ደግሞም ብዙውን የሚተው ተብሎለታል፤ ታዲያ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አሁን የሌለ የመጽሐፉ ሰዎች የሸሸጉት ነገር ግን ቁርአን የገለጸው ብዙው ምንድን ነው?
- ለዚህ የቁርአን አያት መውረድ ሰበቡ /ምክንያቱ/ ምንድን ነበር? የቀደሙት የእስልምና ምሑራን ስለዚህ ጉዳይ ምን ብለዋል?
- ሁኔታው እውን መጽሐፍ ቅዱስ የተበረዘ መሆኑን ያመለክታል? በዚህስ የማን ታማኝነት ይሆን ጎልቶ የሚታየው?

# አስባብ

**ኢብን አባስ እንዲህ ብሏል**፡- "(የመጽሐፉ ባለቤቶች ሆይ! መልክተኛችን) ማለት ሙሐመድ (በእርግጥ መጣላችሁ፣ ከመጽሐፉ ትሸሽጉት ከነበራችሁት ነገር ብዙውን ለእናንተ የሚገልጽ) ማለት ስለ ነቢዩ ሙሐመድ ባህሪና መገለጫ እና አመንዝራን በድንጋይ ስለመውገር የተላለፉትን ሕጋዊ መመሪያዎች እንዲሁም ሌሎች ነገሮችን የምትሸሽጉትን ማለት ነው" በማለት አብራርቷል፡፡

**ኢማም ኢብን ካሲርም**፡- "አል-ሃኪም በራሱ የሐዲስ ስብስብ እንዳሰፈረው ኢብን አባስ እንዲህ አለ፡- “አመንዝራን ወግሮ በመግደል የሚክድ ሰው ሳያውቀው በቁርአን ይክዳል፤ አላህ እንዲህ እንዳለው፡- ‘የመጽሐፉ ባለቤቶች ሆይ፤ ከመጽሐፉ ትሸሽጉት ከነበራችሁት ነገር ብዙውን ለእናንተ የሚገልጽ፣ መልእክተኛችን (ሙሐመድ) በእርግጥ መጣላችሁ’ እናም አመንዝራን በድንጋይ ወግሮ መግደል ከሚደብቋቸው ነገሮች መካከል ነው፡፡” አል-ሐኪምም ይህ ትክክለኛ የሆነ የሐዲስ ሰንሰለት ነው እነርሱ ግን አልጻፉትም አለ፡፡"

# ለዚህ ክስ መጠየቅ ያለብን ጥያቄዎች?

1. በመጀመሪያ ተሸሸጉ ማለት ምን ማለት ነው? አውጥታችሁ ጣላችሁት ማለት ካልሆነ፣ አንቀጹ መጽሐፍ ቅዱስ ስለመበረዙ እንደማስረጃ ሆኖ ሊጠቀስ እንዴት ቻለ? ደግሞስ እነዚህ ሸሽጋችኋቸው የተባሉት ህግጋት አሁን ባለው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሉምን?
2. ቁርአን የተሸሸገውን ገላጭ መጽሐፍ ከሆነ የመጽሐፉ ሰዎች የሸሸጉት የተባለው አመንዝራን በድንጋይ ወግሮ በመግደል መቅጣትን የሚያዘው የሕግ አንቀጽ ቁርአን ውስጥ አለን?
3. ነቢዩ ሙሐመድ በአምንዝራውና በአመንዝራው ላይ ፍርድ ሲያስተላልፉ የቁርአን አንቀጽ ወርዶላቸው እንዳልነበር ይታውቃል፡፡ ፍርዱ የተላለፈባቸው ተውራቱ ላይ በሰፈረው ፍርድ መሠረት ሆኖ ሳለ የምትሸሽጉትን ገላጭ እንዴት ይልላ?

# ከቁርዓን ውስጥ የጠፉት ህግጋቶች

ሱና ኢብን ማጃህ ቅጽ 3፣ 1944 አኢሻህ እንዲህ አለች፡- "**የአመንዝራን በድንጋይ ወግሮ መግደልና አዋቂን አስር ጊዜ ጡት የማጥባት አንቀጽ ወርዶ ነበር**፤ ወረቀቱም እኔ ዘንድ ከትራሴ ሥር ነበር፡፡ የአላህ መልእክተኛ በሞቱ ጊዜ በሞታቸው ተጨንቀን ሳለን በግ ገብታ በላችው፡፡" ሐዲሱ ሃሳን ነው

# ቃላትን ከስፍራው መቀየርና ምላስን ማጣመም

አንቀጾች ሱረቱል አሊ-ኢምራን 3 ፡ 78

ከእነሱም እርሱ ከመጽሐፉ ያይደለ ሲኾን ከመጽሐፉ መኾኑን እንድታስቡ በመጽሐፉ **ምላሶቻቸውን የሚያጣምሙ** ክፍሎች አሉ፡፡ እርሱ ከአላህ ዘንድ ያልኾነ ሲኾን «እርሱ ከአላህ ዘንድ ነውም» ይላሉ፡፡ እነርሱ የሚያውቁ ሲኾኑም በአላህ ላይ ውሸትን ይናገራሉ፡፡

አል-ማኢዳ 5 ፡ 41

አንተ መልክተኛ ሆይ! እነዚያ በክሕደት የሚቻኮሉት ከእነዚያ ልቦቻቸው ያላመኑ ሲኾኑ በአፎቻቸው «አመንን» ካሉትና ከእነዚያም አይሁድ ከኾኑት ሲኾኑ አያሳዝኑህ፡፡ (እነርሱ) ውሸትን አዳማጮች ናቸው፡፡ ለሌሎች ወዳንተ ላልመጡ ሕዝቦች አዳማጮች ናቸው፡፡ **ንግግሮችን ከቦታቸው ሌላ ያጣምማሉ**፡፡ «ይህንን (የተጣመመውን) ብትሰሰጡ ያዙት፡፡ ባትሰሰጡትም ተጠንቀቁ» ይላሉ፡፡ አላህም መፈተኑን የሚሻበትን ሰው ለእርሱ ከአላህ (ለመከላከል) ምንንም አትችልም፡፡ እነዚህ እነዚያ አላህ ልቦቻቸውን ማጥራትን ያልሻላቸው ናቸው፡፡ ለእነርሱ በቅርቢቱ ዓለም ውርደት አላቸው፡፡ ለእነርሱም በመጨረሻይቱ ዓለም ከባድ ቅጣት አላቸው፡፡

# አስባብ

የቁርአን አንቀጾች የወረዱበትን ምክንያት የሚዘግበው አስባብ አል-ኑዙል ሱረቱል አል-በቀራ 2 ፡ 75፣ ሱራ 3 ፡ 78፣ ሱራ 5 ፡ 41 የወረዱት ካብ ኢብን አል-አሽራፍ፣ ራፊ፣ ኪናናህ ኢብን አቡ-ሃቃይቅና ሁያይ ኢብን አህታብ የተባሉ የመዲና አይሁዶች በነቢዩ ሙሐመድ መገለጫ እና አመንዝራን በድንጋይ ወግሮ መግደልን በሚያዘው የተውራቱ ህግ ላይ ስለፈጸሙት ለውጥ እንደሆነ ያትታል፡፡

# የቀጠለ......

- ሁለቱ ጃላላዎችም ለሱራ 2 ፡ 75፣ 3 ፡ 78፣ 4 ፡46 እና ለሱራ 5፡ 41 በሰጡት ማብራሪያ ከላይ ስማቸው የተጠቀሰ የመዲና አይሁዶች በተውራቱ የነቢዩ ሙሐመድን መገለጫ ማጣመማቸውና ራኢና የሚል በአረብኛና በአራማይስጥ የተለያየ ትርጉም ያለውን ቃል በመናገር ያፌዙ እንደነበር፣ እንዲሁም አመንዝራን በድንጋይ ወግሮ ስለመግደል የሚያዘውን ደግሞ በሃይባር የሚኖሩና ቤይኑ ቁሬይዛ የተባሉት አይሁዶች ስለመደበቃቸው ይናገራል በማለት ማብራሪያቸውን ጽፈዋል፡፡107

# የታሪኩ ሙሉ ይዘት

- ሱና ማሊክ ሙዋታ 41 ፡ 1
- ሳሂህ ሙስሊም ቅጽ 4፣ 4437 ገጽ 474-475
- ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ 8፣ 82 ፡ 809

በዝሙት ኀጢአት የተከሰሱ አይሁድና አይሁዳዊት ወደ አላህ መልእክተኛ አቀረቡ፡፡ ነቢዩም እንዲህ ሲሉ ጠየቋቸው፤ በእናንተ በተወረደው በተውራቱ ለእንዲህ አይነት ኀጢአት የተወሰነው ቅጣት ምንድን ነው? ሲመልሱም ቀሳውስቶቻችን ቅጣቱን የገለጹልን ጥላሸት ፊታቸውን በመቀባት ማዋረድ ነው፤ አሉ፡፡ አብዱላ ኢብን ሰላማ "የአላህ መልእክተኛ ሆይ፤ ተውራቱን እንዲያመጡ ንገሯቸው" አለ፤ ተውራቱም 68 መጣ፡፡ አንድ አይሁዳዊ በድንጋይ ተወግሮ እንዲገደል በሚያዘው የአምላክ ቃል ላይ በእጁ በመሸፈን ምን እንደሚል ከፊት ያለውንና ከኋላ የሚከተለውን ማንበብ ጀመረ፡፡ ያኔ ኢብን ሰላማ አይሁዳዊውን እጅህን አንሳ አለው፡፡ በድንጋይ በመወገር መቅጣት የሚያዘው የአላህ ቃል ከእጁ በታች እንደነበር አየ፡፡ የአላህ መልእክተኛም ሁለቱ ኀጢአተኞች በድንጋይ እንዲወገሩ አዘዙ፤ ተወገሩም፡፡ ኢብን ኡመርም በተጨማሪ ሁለቱ ሲወገሩ፣ እንኪሞቱ አይሁዳዊው አይሁዳዊቷን ሲሸፍናት አይቻለሁ አለ፡፡ ኢብን ኡመር የተናገረው ሐዲስ

# የመጽሀፍ ቅዱስ አለመበረዝ ቁርዐናዊ ማሳያ

አል-ሀኪም ሲናገር ጁባይር ቢን ኑፋይር እንዲህ አለ፡- አንዴ ሐጅ ፈጸምኩና አይሻን ጎበኘኋት፤ እርሷም እንዲህ አለችኝ፡- ጁባይር ሆይ አል-ማኢዳህን አንብበሃል ወይንም በቃልህ ሸምድደኸዋል? እኔም አዎን ስል መለስኩላት፡፡ እርሷም እርሱ በመጨረሻ የወረደ ሱራ ነው፡፡ ስለዚህ በእርሱ ውስጥ የምታገኘው የተፈቀደ ማንኛውም ነገር እንደተፈቀደ አስብ፤ ደግሞም ያልተፈቀደ ሆኖ የምታገኘው ማንኛውም ነገር እንዳልተፈቀደ አስብ አለችኝ አለ፡፡

# ሱረቱል አል-ማኢዳህ ምን ይላል?

እነርሱም ዘንድ ተውራት እያለች በውስጧ የአላህ ፍርድ ያለባት ስትኾን እንዴት ያስፈርዱሃል! ከዚያም ከዚህ በኋላ እንዴት ይሸሻሉ! እነዚያም በፍጹም ምእምናን አይደሉም፡፡ እኛ ተውራትን በውስጥዋ መምሪያና ብርሃን ያለባት ስትኾን አወረድን፡፡ እነዚያ ትዕዛዝን የተቀበሉት ነቢያት በእነዚያ አይሁዳውያን በኾኑት ላይ በርሷ ይፈርዳሉ፡፡ ሊቃውንቱና ዐዋቂዎቹም ከአላህ መጽሐፍ እንዲጠብቁ በተደረጉትና በርሱም ላይ መስካሪዎች በኾኑት (ይፈርዳሉ)፡፡ ሰዎችንም አትፍሩ፡፡ ፍሩኝም፡፡ በአንቀጾቼም አነስተኛን ዋጋ አትለውጡ፡፡ አላህም ባወረደው ነገር ያልፈረደ ሰው እነዚያ ከሓዲዎቹ እነርሱ ናቸው፡፡

# የቀጠለ......

- በእነርሱም ላይ በውስጧ «ነፍስ በነፍስ ዓይንም በዓይን አፍንጫም በአፍንጫ ጆሮም በጆሮ ጥርስም በጥርስ (ይያዛል)፡፡» ቁስሎችንም ማመሳሰል አለባቸው ማለትን ጻፍን፡፡ በእርሱም የመጸወተ (የማረ) ሰው እርሱ ለርሱ (ለሠራው ኃጢአት) ማስተሰሪያ ነው፡፡ አላህም ባወረደው ነገር የማይፈርድ ሰው፤ እነዚያ በደለኞቹ እነርሱ ናቸው፡፡ በፈለጎቻቸውም (በነቢያቶቹ ፈለግ) ላይ የመርየምን ልጅ ዒሳን ከተውራት በስተፊቱ ያለውን አረጋጋጭ ሲኾን አስከተልን፡፡

# የቀጠለ......

- ኢንጂልንም በውስጡ ቀጥታና ብርሃን ያለበት በስተፊቱ ያለችውን ተውራትንም የሚያረጋግጥ ለጥንቁቆችም መሪና ገሳጭ ሲኾን ሰጠነው፡፡ የኢንጅልም ባለቤቶች በውስጡ አላህ ባወረደው ሕግ ይፍረዱ፡፡ አላህም ባወረደው የማይፈርድ ሰው እነዚያ አመጸኞች እነርሱ ናቸው፡፡
- ወደ አንተም መጽሐፉን ከበፊቱ ያለውን መጽሐፍ አረጋጋጭና በእርሱ ላይ ተጠባባቂ ሲኾን በእውነት አወረድን፡፡ በመካከላቸውም አላህ ባወረደው ሕግ ፍረድ፡፡ እውነቱም ከመጣልህ በኋላ ዝንባሌዎቻቸውን አትከተል፡፡ ከእናንተ ለሁሉም ሕግንና መንገድን አደረግን፡፡ አላህም በሻ ኖሮ አንድ ሕዝብ ባደረጋችሁ ነበር፡፡ ግን በሰጣችሁ ሕግጋት ሊሞክራችሁ (ለያያችሁ)፡፡ በጎ ሥራዎችንም (ለመሥራት) ተሽቀዳደሙ፤ መመለሻችሁ በጠቅላላ ወደ አላህ ነው፡፡ በእርሱም ትለያዩበት የነበራችሁትን ነገር ይነግራችኋል፡፡

# መቋጫ

- በሱረቱል አል ማኢዳህ እንዲሁ በሻሪና ተሻሪ ህግ መሰረት  ማንኛውም ሙስሊም መጽሀፍ ቅዱስ ተበርዟል ማለት አይችለም